ጉባዔ ሁለት::

ኦ ማርያም በእንተዝ ናፈቅረኪ ወናዐብየኪ::

ኦ ቃለ አክብሮ፣ ቃለ አፍቅሮ፣ ቃለ አራኅርኖ፣ ቃለ አሕሥሮ ይሆናል:: ቃለ አራኅርኖ ኦ ድንግል አዘክሪ ኀበ መዘክር፣ ኦ ዮሴፍ ያለው ነው:: ቃለ አሕሥሮ ኦ ይሁዳ በስኢምኑ ታገብኦ ለወልደ እጓለ እመሕያው[15]፤ ኦ ሐናንያ እፎ መልአ ሰይጣን ውስተ ልብከ ከመ ተሐሥዎ ለመንፈስ ቅዱስ[16] ያለው ነው:: ቃለ አክብሮ ኦ አኀው ፍቁራን፣ ኦ ድንግል ምልዕተ ውዳሴ ኦ ጳውሎስ ያለው ነው:: መጽሐፍ ያለፈውንም የሚመጣውንም ማጻፍ ልማድ ነውና፤ እመቤታችን! ስለዚህ እንወድሻለን እናከብርሻለን እናገንሻለን:: አሁን እመቤታችንን የምናገናት ሆና አይደለም ክብርሽን ገናንነትሽን እንናገራለን ሲል ነው::

እስመ ወለድኪ ለነ መብልዐ ጽድቅ ዘበአማን ወስቴ ሕይወት ዘበአማን::

እውነተኛውን ምግብ እውነተኛውን መጠጥ ኢየሱስ ክርስቶስን አስገኝተሽልናልና:: ዘበአማን አለ ከዚህ ዓለም መብል መጠጥ ሲለይ፤ የዚህ ዓለም መብል መጠጥ ማታ በልተውት ጠጥተውት ለጠዋት፣ ጠዋት በልተውት ጠጥተውት ለማታ ያሻል:: ይህ ግን በሚገባ ከተቀበሉት ሕማሙንና ሞቱን ለማዘከር ነዉ እንጂ አንድ ጊዜ ከተቀበሉት በሌላ ጊዜ አያሻምና፤ አንድም በኀጢአት ካላሳደፉት በስተቀር ለዘላለሙ ጸጋ ክብር ሲሰጥ ይኖራልና:: አንድም ከመሥዋዕተ ኦሪት ሲለይ ነው:: ያ ሥጋዊ ይህ መንፈሳዊ ነው፣ ያ አፍአዊ ይህ ውሳጣዊ ነው፣ ያ ምድራዊ ይህ ሰማያዊ ነውና:: አንድም የዚህ ዓለም ምግብ ዐሠር ገለባ ይሆናል ይለወጣል በዚህ ግን ይህ ሁሉ የለበትም:: አንድም የዚህ ዓለም ምግብ ሞትን ያስከትላል ይህ ግን የዘለዓለም

---

15 ይሁዳ! በመሳም የሰውን ልጅ አሳልፈህ ትሰጠዋለህን ሉቃስ ፳፪ ፡ ፵፰

16 ሐናንያ ሆይ መንፈስ ቅዱስን ትክደው ዘንድ የቦታህንም ዋጋ ከፍለህ ትደብቅን ዘንድ ሰይጣን በልብህ እንዴት አደረ:: የሐዋርያት ሥራ ፭ ፡ ፫

ሕይወት ይሆናልና። አንድም ከአማናዊቷ እመቤታችን ስለተገ
መብልዐ ጽድቅ ዘበአማን ወስቱ ሕይወት ዘበአማን አለ።

ኦ አበዊነ ንቡራነ እድ ሥዩማን እለ መትልወ ሐዋርያት።

ናፈቅረክሙ ወናዐብየክሙ ሲል ነው አንተጽ ተስማሚውን ያወርዳል።
ተውህበ ጳውሎስ መቁሕ ወካልኢሃ መቁሐን ባለ ጊዜ ተውህቦ።
አገብኣ ለኤልዛቤል ውስተ ምስካባ ዘቀዳሚ ወለአለሂ ዘመዉ ምስሌሃ
ባለ ጊዜ አገብአመ። ትኤምኅክሙ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንተ
ውስተ ባቢሎን ዘግብጽ ብሎ ወማርቆስ ወልድየ ባለ ጊዜ
ይኤምኅክሙ[17] እንዳለበት። ከሐዋርያት ቀጥላችሁ ሐዋርያትን
መስላችሁ በአንብሮተ እድ የምትሾሙ በአንብሮተ እድ የምትሾሙ
አባቶቻችን! እናገናችኋለን፤ እናከብራችኋለን። አንድም ሐዋርያትን
በስም የምትመስሉ በግብር የምትከተሉ አባቶቻችን! እናከብራችኋለን
እናገናችኋለን። ከሊቀ ጳጳስ ጀምሮ እስከ ቄስ ያሉት በአንብሮተ እድ
ይሾማሉ ቅብዓት ያለበት ነው ዲያቆን ግን በአንብሮተ እድ ይሾማል
ቅብዓት የለውም ከዚያ በታች ያሉትን በቃል ይሾሟቸዋል።

እስመ ነሣእናክሙ አስተብቍዕያነ ለነ ለኀበ እግዚአብሔር።

ወደ እግዚአብሔር በአማላጅነት አድርገን ተቀብለናችኋልና። አንድም
አስተብቁዓነ ይላል መልሰን መላልሰን ግብር ጉበተን ተቀብለናችኋልና
እናከብራችኋለን በሀገራቸው ልማድ ተናግሮታል፤ በሀገራቸው ሊቀ
ጳጳሱ የሞተ እንደሆነ የበቁ ደጋጎቹን አባቶች መርጠው ስማቸውን
በቅፋፍ ጽፈው በከርሠ ሐመሩ ውስጥ አኑረው፤ ላለፈው ኦ እግዚኦ
አዕርፍ ነፍሰ አቡነ እገሌ፤ ለሚመጣው ኦ እግዚኦ አንብር ለነ ዲበ
መንበሩ ህየንቱሁ ኖላዌ ኄረ ኢንኩን ከመ መርዔት ዘአልቦ ኖላዊ
ወከመ ኢይምስጠነ ተኵላ መሳጢ እያሉ ሰባት ቀን ይጸልዩበታል፤
ቀኖናው ሲፈጸም አባዬ እማዬ ማለት የማይችል ትንሽ ብላቴና
አምጥተው አንሥተህ ስጠን ይሉታል፤ እያነሣ ይሰጣቸዋል ሳያይ
ይቀላቅሉታል አንዱን መላልሶ የሰጣቸው እንደሆነ አክሶስ አክሶስ
ብለው ይሾሙታል፤ ይደልዎ ይደልዎ ማለት ነው። እየለዋወጠ
የሰጣቸው እንደሆነ ተመልሰው ሰባዔ ይገቡበታልና እንዲህ አለ። ይህ
ሥርዐት ከሐዋርያት ሲወርድ ሲያያዝ የመጣ ነው ይሁዳ በወጣ ጊዜ

[17] የሐዋርያት ሥራ ፲፮ ፥ ፴፫ ፤ ፩ኛ ጴጥሮስ ፭ ፥ ፲፫፤ ራእየ ዮሐንስ ፪ ፥ ፳፩

በይሁዳ እግር እኛ ባወቅን ማትያስንና በርናባስን መርጠናል አንተ ግን ኩላሊት ያጤስውን ልቡና ያመላለስውን መርምረህ የምታውቅ ማእምረ ልብ ነህና ይህቺን የሐዋርያትን ሹመት ገንዘብ የሚያደርጋትን ከእነዚህ ከሁለቱ የመረጥከውን አንዱን ግለጥልን ብለው ዕጣ ቢያጣጥሏቸው ዕጣው ለማትያስ ወጣ፤ አሁን ሐዋርያት የበቃውንና ያልበቃውን የሚያውቁ ሆነው አይደለም ቃል ለቃል ተጨዋውተው መማለጃ ተቀብለው የሥጋ ዝምድና ኖሯቸው ይሆናል ይሉናል ብለው ሐገዘቡ በሐሜት እንዳይጎዱ ነው። አንድም ሁለቱም የበቁ እንደ ሆነ በዕጣ አድርጉ ለማለት ለአብነት ነው። ወተጐለቁ ምስለ አሠርቱ ወአሐዱ ሐዋርያት ከዐሥራ አንዱ ሐዋርያት ዐሥራ ሁለተኛ ሆኖ ተቍጥሯልና እንዲህ አለ።

ወነሣእናሆሙ በመዋዕሊነ አስተብቍዕ ኀ ሰነ ለንበ እግዚአብሔር አሎንተ ክልኡተ ሊቃነ ጳጳሳት።

የእስክንድርያ ሊቃነ ጳጳሳት እለእስክንድሮስና አትናቴሞስን ሊያማልዱን ባለ በዘመናችን ተቀብለናቸዋልና፤ አንድም ጳጳሳትና ሊቃነ ጳጳሳትን ባለ በዘመናችን ወደ እግዚአብሔር አማላጅነት ተቀብለናቸዋልና፤ ነሣእናሆሙ ካለ ለአሎንቱ አሎንተም ካለ ነሣእነ ባለ በቀና ነበር ልማደ መጽሐፍ ነው፤ ዘንተ ቃለ ንሕነ ሰማዕናሁ ከመ እምሰማይ ወረደ እንዘ ሀሎነ ምስሌሁ ውስተ ደብረ መቅደሱ እንዲል። ምነው ሊቀ ጳጳሳት ብለው አንድ አይደለምን ሊቃነ ጳጳሳት ብሎ አበዛ ቢሉ መጽሐፍ ስም ካልጠራ ማብዛት ልማድ ነው በተአምኖ አመ ነገርዎ ለኖኅ፤ ብዕዕት አንቲ እንተ ተአምኒ ከመ ይከውን ቃል ዘነገሩኪ እምኀበ እግዚአብሔር እንዲል።[18]

አንድም በመዲናዩቱ በእስክንድርያ የተሾሙትን እሊህን አባ እለ እስክንድሮስን አባ አትናቴሞስን ግብር ገብተን ከእግዚአብሔር አግኝተን ተቀብለናቸዋልና እናከብራቸዋለን እናገናቸዋለን፤ ሁለቱን አኀው እለእስክንድሮስ ተከራክሮ አርዮስን ረትቶልናልና፤ አትናቴሞስ በእሱ ጸሎት በእሱ ዘመን አርዮስ ሞቶልናልና። አንድም በመዲናዩቱ በእስክንድርያ የተሾመ አባ እለእስክንድሮስን በሀገራችን መዲና በአክሱም የተሾመ አባ ሰላማን ግብር ገብተን ከእግዚአብሔር አግኝተን

[18] ከእግዚአብሔር ተልከው የነገሩሽ ቃል እንደሚሆን የምታምኚ አንቺ ብዕዕት ነሽ። ሉቃስ ፩ ፥ ፵፭

ተቀብለናቸዋልና እናከብራቸዋለን እናገናቸዋለን። ይህስ እንደምንድን
ነው ቢሉ መረጻዎስ የሚባል ነጋዴ ሲድራኮስና ፍሬምናጦስ የሚባሉ
ሁለት ብላቴኖች አስከትሎ ወደ ሀገራችን መጥቶ ሳለ እሱ ሞተ።
ሲድራኮስ ቤተ መዛግብት ገባ ፍሬምናጦስ የአክሱሙ ገበዝ እንበረም
ይባላል ከእሱ ዘንድ ብሉይ ሲማር ኖረ። ሥርዓታቸውን አይቶ አንሰ
አነክር ግብረክሙ ኦ ሰብአ ኢትዮጵያ እናንተ የኢትዮጵያ ሰዎች
ሥርዓታችሁን እያየሁ አደንቃለሁ ግዝረት ወእምነተ ክርስቶስ ብክሙ
ተገዝራችኁል አምናችኁል ጥምቀትሰ ወቆሪበ ቁርባን አልብክሙ
የማትጠመቁ ሥጋውን ደሙን የማትቀበሉ ስለምንድን ነው? አላቸው
ግዝረተ አምጽኡ ለነ ሌዋውያን አበዊነ ግዝረትን ሌዋውያን አባቶቻችን
አምጥተውልን ተገዝረናል። እምነተኒ አምጽአ ለነ ሐጽዋ ለሐንደኬ
እምነትንም ባኮስ የተባለ የሐንደኬ ባለሟል አምጥቶልን አምነናል።
ለዝሰ ኢተፈነወ ለነ ሐዋርያ ጎቤነ እምጎቤሆሙ ለእዚህ ግን መምህር
ባይመጣልን ነው አሉት። እስክንድርያ ቅርብ ናት ሄዳችሁ
አታመጡም? አላቸው። የወዲሁንም የወዲያኛውንም ቋንቋ የምታውቅ
አንተ ነህና ሄደህ አምጣልን ብለው አምስት መቶ ወቄት ወርቅ ስንቅ
ሰጥተው ላኩት። እሱም ተነሥቶ እስክንድርያ በወርዱ
እለእስክንድሮስን አጣው ቢጠይቅ ለአውግዙተ አርዮስ ኒቅያ ሄዷል
አሉት። ተከትሎ ቢሄድ ሠለስቱ ምእት ሥርዓት ሠርተው ሲለያዩ
እለእስክንድሮስን ከበሩ አግኝቶ የኢትዮጵያ ሰዎች ልከውኛል ብሎ
ነገሩን አስረዳው ደግ ሰዓት ላይ ደርሰሃል። ይህንንስ እኔ ብቻዬን
የማደርገው አይደለም ብሎ ተመልሶ ሠለስቱ ምእትን ኢትዮጵያ
የምትባል ያለ ሐዋርያ ያመነች ሀገር አለች አላቸው። ደግ ነው ለአንተ
ሀገር አቅራቢያ ናትና አንተው ባወቅህ ሹምላት በስምንተኛው መንበር
ይቀመጥ ብለው ሥርዓት ሠርተዋል። እሱም ከአባ እለእስክንድሮስ
ዘንድ ሦስት ወር እንደተማረ አባ እለእስክንድሮስ ሞቶ አትናቴዎስ
ተሾመ። ከእርሱም ዘንድ አምስት ዓመት ሐዲስ ተምሮ ኤጲስ ቆጶስነት
ተሾሞ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ ወሰበከ በብሔረ አግዓዚ ይላል
ወንጌልን አስተምሯልና።

አንድም በሀገራችን መዲና የተሾሙ ሊቃነ ጳጳሳት አባ ዕገሌንና አባ
እገሌን ግብር ገብተን ከእግዚአብሔር አግኝተን ተቀብለናቸዋልና

እናከብራቸዋለን፤ ጸሐፊ የጊዜውን ይጽፋል አንባቢም የጊዜውን ያነባል ተርጓሚም የጊዜውን ይተረጉማል።

አንድም የሀገራችንን ሊቀ ጳጳሳት ከእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ አስጠግቶ ስምዖንን ከሌዊ አስጠግቶ ካህን እንዳለው። ካህናት ጎሉፋን ፍና ከበቱ ፍኖተ እግዚአመ አመ ቀተልዋ ለሰቂማ እስመ ዐመሳ ገብሩ ቤተ እስራኤል እንዲል።[19] አንድም ከወንበሩ አስቀምጦ መስቀሉን አሰሠ እሱን የሚሾመው ስለሆነ። አንድም ስም ሰጥተው ግብር ነሥተውታል። በእስክንድር እስክንድርያ ተብላለች በቂሣር ቂሣርያ በኤቦር ዕብራውያን በይሁዳ አይሁድ እንደ ተባሉ። ይህስ እንደምንድን ነው ቢሉ እስክንድር የተባለ ጥበበኛ ንጉሥ ነበር መንግሥት ለማዳረስ ግብር ለማስገበር ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ፤ ቀድሞ የሀገራችን ነገሥታት አክሱም ወጥተው መንግሥት ያደርሱ እንደ ነበር። አንድም ያቱም በለዝን ተጠግቶ ለመመለስ፤ ያቱም በለዝን ተጠግቶ ሲመለስ ከዚች ሀገር ደረሰ፤ ይህች ሀገር ቀድሞ ማይ ጽርሐ ማይ ጽንፋ ትባል ነበር። እስክንድርም ስሜን የሚያስጠራ ልጅ የለኝም ስሜን የሚያስጠራ ለመታሰቢያ የሚሆን ምን ባደርግ ይሻላል ብሎ መሳፍንቱን ቢያማክር ይህቺን በውኃ የተከበበች ሀገር ደልድለህ ሠርተኽ ስምህን አስጠራ አሉት። እሱም ውኃውን በመዘውር መልሶ ብርሃን የማይከለክል ውኃ የሚከለክል ልብስ አለ ያንን እየለበሰ የብረት መሰላል (አምድ) እየተከሰ የብረት ርብራብ እየጣለ የብረት ድልድይ እየደለደለ የብረት ሠረገላ እያሽጋገረ ሠርቶታል። የባሕር አራዊት (ጉማሬ) እንዳያፈርሱት ገባሬ ተአምራት የሆነ ዐፅመ ኤልሳዕን አኑሮበታል፤ ቴዳ ቴዳ የሚል ሦስት ድስት ምሉእ ወርቅ ቀብሮበታል። ከዚህ በኋላ ምኩራበ ጣዖት ሆኗል። አንድም የጥራጊ ማፍሰሻ ሁኗል። ይህ የተደረገው በዘመነ ብሉይ ነው፤ ሲወርድ ሲያያዝ ከዘመነ ሐዲስ ደረሰ ሲያያዝ ከዘመነ ሊቃውንት ደረሰ። አትናቴዎስ በእስክንድርያ ተሾሞ ሳለ በዘመኑ ጽኑዕ ረኃብ ሆነ፤ ወርቅ ከዚህ ውስጥ ተቀብሮ እንዴት ነዳያን በረኃብ ይመቱ እያለ ያዝናል። እምከመ ረከብኩ ሞገሰ በቅድመ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ኢየኅድጎ ለዝንቱ አድራማሌክ እያለ ሲያስብ ተምኔቱ ሳይፈጸምለት ዐረፈ። ከእሱ ቀጥሎ አባ ቴዎፍሎስ ተሾሟል፤ በእሱም ዘመን ረኃብ

---

[19] ጎዳናን የሚያልፉ ካህናት ግን በእስራኤል ወገን ላይ በደልን ሠርተዋልና ሰቲማን በገደሏት ጊዜ የጌታቸውን መንገድ ሸሹ። ሆሴዕ ፮ ÷ ፱

ሆነ፤ እሱም እንደ አትናቴዎስ ወርቅ ከዚህ ውስጥ ተቀብሮ እንዴት ነዳያን በረኃብ ይሙቱ እያለ ሲያዝን ኤራርታ የምትባል የሴት ወይዘሮ ሠራዊቷን አስከትላ መጣች፤ ስለምን ቢሉ ምናኔ ሽታ፤ ሠራዊቷንስ አስከትላ ምናኔ አትሄድም ብሎ ገዳማተ ግብጽን እጅ ለመንሣት፤ አንድም ከአበው ለመባረክ፤ ከአበው አንዱ እሱ ነውና ብትሄድ ቴዎፍሎስ አዝኖ ተክዞ አገኘችው፡፡ አባቴ! ምን ሆነህ አዝነሃል? አለችው፡፡ ወርቅ ከዚህ ውስጥ ሞልቶ ነዳያን ሲሞቱ እንደምን አላዝን አላት፤ ምነው ታድያ አታስቆፍረውም? አለችው ባይሆንልኝ ነዋ አላት፤ ይህ ከሆነ የሚያስጨንቅህ ባንተ ጸሎት በእግዚአብሔር ቸርነት አስቆፍሬ አወጣልሃለሁ ብላ አውጥታለታለች፡፡ ቴዳ ቴዳ ያለውን ይተረጉማል፡፡ አንዱ ቴዳ በዚያን ዘመን ዘየዐቢ ቴዎዶስዮስ ነግሦ ነበርና ለእሱ ሰዶለታል፡፡ ንጉሡም አባቴ! እኔ ላንተ መስጠት ሲገባኝ አንተ ለእኔ ትሰጠኛለህን? ብሎ ለበረከት ያህል አስቀርቶ መልሶ ልኮለታል፡፡ አንዱ ቴዳ ታዖስ የሚል ነው ይህ የአምላክ ገንዘብ ነው ብሎ ለነዳያን መጽውቶታል፤ አንዱ ቴዳ ቴዎፍሎስ የሚል ነው ይህ የእኔ ገንዘብ ነው ብሎ ከፍሎ መጽውቶ ከፍሎ አብያተ ክርስቲያናትን አሠርቶበታል፡፡ እነዚህም አብያተ ክርስቲያናት ታቦተ ኢየሱስ፣ ታቦተ ማርያም፣ ታቦተ ሚካኤል፣ ታቦተ ዮሐንስ መጥምቅ፣ ታቦተ ኤልሳቤጥ፣ ታቦተ ኤልሳዕ፣ ታቦተ መርቆሬዎስ፣ ታቦተ ሩፋኤል ናቸው፡፡ ታቦተ ሩፋኤል በዘባነ አንበሬ የታነጸው በዚያን ጊዜ ነው፡፡ ወርቅ ስለተገኘባት ዐባይ ሀገር አላት፤ ይህስ አባ ሕርያቆስ የሚሻ የሥጋው የደሙ ነገር ነው፤ መንፈሳዊ ነገር ሊናገር መጥቶ ማሩን አምርሮ ወተቱን አጥቁሮ ሥጋዊ ነገር ወርቅ ብር ተገኘባት ብሎ ዐባይ ሀገር አይላትም ብሎ፤ ወትከውን አሐቲ ሀገር ምሥዋዖ ለእግዚአብሔር[20] ካላቸው አንዲቱ እሷ ናትና፡፡ አንድም ርእሰ አክሱም ወልደ አግዓዚ ምኒልክ ነግሦባታልና፤ አንድም በአራቱ ማዕዘን ሃይማኖት ሲጠፋ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ ወልድ ዋሕድ ስትል ትኖራለችና ሀገር መላ ኢትዮጵያ፡፡

---

[20] በግብጽ ምድር መካከል አንዲቱ ከተማ ለእግዚአብሔር መሠዊያ ትሆናለች፡፡ ኢሳይያስ ፲፱ ፡፲፱

ይ.ዲ. በእንተ ብፅዕት፡፡

ዲያቆኑ ብፅዕት አንቲ እንተ ተአምኒ ከመ ይከውን ቃል ዘነገሩኪ እምኀበ እግዚአብሔር ተብላ በኤልሳቤጥ ቃል የምትመሰገን እመቤታችንን አማላጅ በማድረግ በእሷ አማላጅነት ስለእሷ ብለህ ማረን ይቅር በለን ራራልን ይበል፡፡

ወፍሥሕት፡፡

በመልአኩ ቃል ተፈሥሒ ፍሥሕት ተብላ የምትመሰገን የደስታ መፍሰሻ የሆነች እመቤታችንን አማላጅ በማድረግ በእሷ አማላጅነት ስለእሷ ብለህ ማረን ይቅር በለን ራራልን፡፡

ወስብሕት በኵሉ፡፡

ክቡር በውስተ ነቢያት ክቡር በውስተ ሊቃውንት እንዲል ቅጽል ያስቀድማል በውስጥ በአፍአ፣ በነፍስ በሥጋ፣ በመላእክት በደቂቀ አዳም በካልዕ ፍጥረት፣ የተመሰገነች እመቤታችንን አማላጅ በማድረግ በእሷ አማላጅነት ስለእሷ ብለህ ማረን ይቅር በለን ራራልን፡፡

ወቡርክት፡፡

ቡርክት አንቲ እምአንስት ተብላ ስለተመሰገነች መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለባት ቦረከተ ሥጋ በደከተ ነፍስን እያማለደች የምታሰጥ እመቤታችንን አማላጅ በማድረግ በእሷ አማላጅነት ስለእሷ ብለህ ማረን ይቅር በለን ራራልን፡፡

ወቅድስት ወንጽሕት፡፡

ንጽሕት ኵሎ ጊዜ ተብላ ስለተመሰገነች አምላክን ስለወለደች ስለእመቤታችን አንድም እሷን አማላጅ በማድረግ ዕጣን ቋጥረው መብዓ ይዘው ግብር ሰፍረው ወደ እግዚአብሔር የሚሄዱትን አስባቸው፤ ንጽሕት ከልማደ አንስት ነው፤ አንድም ከነቢብ ከቃል ከአንደበት ከገቢር ከድርጊት ከኀልዮ ከሐሳብ ንጽሕት የሆነች እመቤታችንን አማላጅ በማድረግ በእሷ አማላጅነት ስለእሷ ብለህ ማረን ይቅር በለን ራራልን፡፡

እግዝእትነ ወላዲተ አምላክ ማርያም ድንግል፡፡

በኅቱም ድንግልና ፀንሳ በኅቱም ድንግልና አምላክን የወለደች እመቤታችንን አማላጅ በማድረግ በእሷ አማላጅነት ስለሷ ብለህ ማረን

ይቅር በለን ራራልን፡፡ እግዝእትነ አለ ከግብርናተ ዲያብሎስ ነጻ አውጥቶ የሚገዛን ከእሷ በነግው ሥጋ ነውና፡፡

ወበእንተ ቅዱሳን ክቡራን ጽኑዓን መንፈሳውያን ረቂቃን ወኃያላን፡፡

ንጹሓን ክቡራን የሚሆኑ መላእክትን አማላጅ በማድረግ በእነሱ አማላጅነት ስለ እነሱ ብለህ ማረን ይቅር በለን፡፡ መንፈሳውያን አላቸው ረቂቃን ናቸውና፡፡ መላእክት አላቸው ማዕረጋቸውን ሲያይ፡፡ ሰማያውያን አላቸው ቦታቸውን ሲያይ፡፡ ኃያላን አላቸው በተፈጥሮ ለመላእክት ኀይል ተሰጥቷቸዋል፤ ኋላም በእርዳታ ምክንያት ሲጨመርላቸው ይኖራልና፡፡ ወነሥአ አሐዱ መልአክ ኃያል ወጽኑዕ ዕብነ ዐቢየ ከመ እንተ ማኅረጽ ወወገረ ውስተ ባሕር ወይቤ ከመዝ ትትገደፍ ባቢሎን ዐባይ ሀገር እንዲል፡፡

ወሰባኪ ነስሑ እስመ ቀርበት መንግሥተ ሰማያት ጸያሔ ፍኖት ዮሐንስ መጥምቅ፡፡

ደጊቱ መንግሥተ ሰማያት በልጅነት ልትሰጥ ቀርባለችና በወንጌል አምናችሁ ንስሐ ግቡ፤ ልቡናችሁን ለእግዚአብሔር ማደሪያነት አሰናዱ፤ ሰውነታችሁን ከኃጢአት ከጣኦት አጽዱ፤ እንቅፋቱን አስወግዱ የእግዚአብሔርን መንገድ ጥረጉ እያለ የሚያስተምር ዮሐንስ መጥምቅን አማላጅ በማድረግ በእሱ አማላጅነት ስለሱ ብለህ ማረን ይቅር በለን፡፡

ወበእንተ ቅዱሳን ስቡሓን ወላእካን ማቴዎስ ወማርቆስ ሉቃስ ወዮሐንስን አርባዕቱ ወንጌላውያን፡፡

ንጹሓን ክቡራን የተመሰገኑ አገልጋዮችህ አራቱን ወንጌላውያን ማቴዎስን ማርቆስን ሉቃስን ዮሐንስን አማላጅ በማድረግ በእነሱ አማላጅነት ስለእነሱ ብለህ ማረን ይቅር በለን፡፡ ማቴዎስ ማለት ኅሩይ እመጸብሓን ማለት ነው፤ ከቀራጭነት ለሐዋርያነት ተመርጧልና፡፡ ማርቆስ ማለት ንህብ ማለት ነው፡፡ ንህብ ሁሉን እንዲቀስም እሱም ቀድሞ ከጌታ ኋላ ከሐዋርያት ተምሯልና፡፡ አንድም ልዑክ ማለት ነው፤ ለስብከተ ወንጌል ይፋጠናልና፡፡ ወአምጽኡ ማሬ ዘድዮስ እንዲል[21]፤ አንድም ማሬ ማርቆስ ይላል የተደራረበ ቀለም ነው መልእክተ ሲኖዲቆን እንዲል፡፡ አንድም አንበሳ ማለት ነው፤ አንበሳ

---

21 በሀገሩ ፊት ለፊት ያለውን የጣዖቱን ካህን ከላሞችና ከመሠውያ ዕቃዎች ጋር ወደ ከተማው በር ከሕዝባቸው ጋር አመጡ፡፡ የሐዋርያት ሥራ ፲፬ ፡ ፲፫

ለላም ጌታው ነው ይሰብረዋል፤ ማርቆስም በግብጽ አምልኮተ ጣዖትን አጥፍቷልና፡፡ ሉቃስ ማለት መበሥር ማለት ነው ብሥራተ መልአክን ይጽፋልና፡፡ አንድም ተንሣኢ ማለት ነው ለስብከተ ወንጌል ይፋጠናልና፡፡ አንድም አቃቤ ሥራይ ማለት ነው ቀድሞ ዐቃቤ ሥራይ ዘሥጋ ኋላ ዐቃቤ ሥራይ ዘነፍስ ሆኗልና፡፡ ዮሐንስ ማለት ፍሥሓ ወሐሤት ማለት ነው፤ ቅብዐ ትፍሥሕት መንፈስ ቅዱስ ያሰጣልና፡፡ ወብዙኃን ይትፌሥሑ በልደቱ እንዲል፡፡[22] አንድም ርኅራኄ ወሣህል ማለት ነው፤ በጸጋ ዘነሣእክሙ በጸጋ ሀቡ በከንቱ ዘነሣእክሙ በከንቱ ሀቡ[23] ባለው ጸንቶ ያስተምራልና፡፡

ወበእንተ ቅዱሳን አግብርቲከ፡፡

እምከመ ገበርክሙ ኵሎ ዘአዘዝኩክሙ ኢይብለክሙ አግብርትየ አላ አዕርክትየ እንዲል[24]፤ ወዳጆቼ ባለሟሎቼ እንጂ ባሮቼ አልላችሁም ያልካቸው ሐዋርያትን አማላጅ በማድረግ በእነሱ አማላጅነት ስለእነሱ ብለህ ማረን ይቅር በለን፡፡ አንድም ክቡራን ባለሟሎችህ ስለሚሆኑ ሐዋርያት ብለህ ማረን፤ አግብርቲከ የባለሟልነት ስማቸው ነው ዳዊት ገብርየ ሙሴ ገብርየ እንዲል፡፡[25]

ጴጥሮስ፡፡

ስለጴጥሮስ ብለህ ማረን ይቅር በለን፡፡ ጴጥሮስ ማለት ትክል ዐለት ማለት ነው፡፡ ያን ዐለት የሌሊት ቁር የመዓልት ሐሩር እንደማይለውጠው ጴጥሮስም በክህደት በኀጢአት አይለወጥምና፡፡ አንድም ሻፎ ስለታም ደንጊያ ማለት ነው፡፡ ያ ስለታም ድንጋይ አጥንቱን ከሥጋ ሥጋውን ከአጥንት እንዲለይ እሱም አማኒውን ከመናፍቅ ጻድቁን ከኀጥእ ለይቶ ያስተምራልና፡፡ አንድም ከዋው ደንጊያ ማለት ነው፡፡ ከዋው ደንጊያ አንድ ጊዜ የጣሉት እንደሆነ እየፈጋ እየተፈናጠረ ከሩቅ ይደርሳል፤ እሱም በዐሥራ ሁለቱ ዕጣ እየገባ ያስተምራልና፡፡ አንድም መርግ ወይም ናዳ ደንጊያ ማለት ነው፡፡ ናዳ ከላይ እየናረ ሲመጣ ያስፈራል ጴጥሮስም ሞተ በሥጋ ወሐይወ

---

22 በመወለዱም ብዙዎች ደስ ይላቸዋል፡፡ ሉቃስ ፩ ፡ ፲፬
23 በከንቱ (በነጻ) የተቀበላችሁትን በከንቱ (በነጻ) ስጡ ማቴዎስ ፲ ፡ ፰
24 እኔ ያዘዝኋችሁን ሁሉ ብታደርጉ ወዳጆቼ ናችሁ እንጂ እንግዲህ ወዲህ ባሮቼ አልላችሁም፡፡ ዮሐ ፲፭ ፡ ፲፬
25 መዝሙር ፹፰ ፡ ፳

በመንፈስ[26] እያለ ስለነገረ ክርስቶስ ሲያስተምር ያስፈራልና፡፡ አንድም መሠረት ማለት ነው፤ወአንሰ እብለከ ከመ አንተ ኰኵሕ ወዲበ ዛቲ ኰኵሕ አሐንጻ ለቤተ ክርስቲያንየ ወአናቅጸ ሲኦል ኢይኄይልዋ እንዲል፡፡[27]

ወያዕቆብ፡፡

ስለያዕቆብ ብለህ ማረን ይቅር በለን፡፡ ያዕቆብ ማለት አዕቃፂ አኃዚ ማለት ነው፡፡ የቀደመው ያዕቆብ አዕቃፄ ሰኰና ኤሳው እንደሆነ ይህም አዕቃፄ ትምህርተ መናፍቃን ነው በትምህርቱ የመናፍቃንን ትምህርት ያሰናክላልና፡፡ አንድም የቀደመው ያዕቆብ ሰኰና ኤሳውን ይዞ እንደተወለደ ይህም ሰኰና ወንጌልን ይዞ በዚያው ሲያስተምር ሞቷልና፡፡ አይሁድ በምዕፃበ ዕፅ ደብድበው ገድለውታል፡፡

ወዮሐንስ፡፡

ስለ ዮሐንስ ብለህ ማረን ይቅር በለን፡፡ ትርጉሙ እንዳለፈው ነው፡፡

ወእንድርያስ፡፡

ስለ እንድርያስ ብለህ ማረን ይቅር በለን፡፡ እንድርያስ ማለት ተባዕ ለመስቀል ማለት ነው፡፡ ወንጌልን ለማስተማር መከራ ለመቀበል ጥቡዕ ነውና፡፡ አንድም በኵረ ሐዋርያት ማለት ነው እስከ ሀገረ በላዕተ ሰብእ ድረስ ሄዶ አስተምሯልና፤ አንድም ከሐዋርያት አስቀድሞ ተመርጧልና፡፡

ፊልጶስ፡፡

ስለ ፊልጶስ ብለህ ማረን ይቅር በለን፡፡ ፊልጶስ ማለት ረያጼ አፍራስ አኃዜ ኵናት ማለት ነው፡፡ አንድም መፍቀሬ አምላክ መፍቀሬ አኃው ማለት ነው ፊልሳዳፎስ እንዲል፡፡

ወበርተሎሜዎስ፡፡

ስለ በርተሎሜዎስ ብለህ ማረን ይቅር በለን፡፡ በር ማለት በዕብራይስጥ ልጅ ማለት ነው፤ ሎሜዎስ ማለት ተክል ማለት ነው፡፡ በርተሎሜዎስ ማለት የአትክልት አጠጭነት ግብር ያለው ልጅ ማለት ነው፡፡ ይኸውም

---

[26] ስለኃጢአታችን በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ነው ፩ኛ ጴጥሮስ ፫ ፡ ፲፰

[27] አንተ ዐለት (መሠረት) እንደሆንክ እኔ እነግርሃለሁ በዚያች ዐለት ላይም ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ የሲኦል በሮችም አይበረቱባትም፡፡ ማቴዎስ ፲፮ ፡ ፲፰

ሊታወቅ ጧት ወይን ተክሎ ለማታ መሥዋዕት አድርሷልና ኩን ወልደ ኀይል ኩን ወልደ የማን እንዲል። አንድም ራሱን እንዳጠፋ ስውነታቸውን እንደ ተክል ልቡናቸውን እንደ ምድር ትምህርቱን እንደ ውኃ አድርጎ መስሎ ያስተምራልና።

ቶማስ።

ስለ ቶማስ ብለህ ማረን ይቅር በለን። ቶማስ ማለት ፀሐይ ማለት ነው። ክልኤቱ አስማቲሁ ለፀሐይ አሐዱ ስመ ቶማስ ወአሐዱ ስመ ኦርያሬስ እንዲል።

ወማቴዎስ።

ስለማቴዎስ ብለህ ማረን ይቅር በለን፤ ወልደ እልፍዮስ ለማለት ደግሞታል ትርጓሜ እንዳለፈው ነው።

ወያዕቆብ።

ስለ ያዕቆብ ብለህ ማረን ይቅር በለን። ትርጓሜ እንዳለፈው ነው፤ ወልደ እልፍዮስ ለማለት ደገመው።

ታዴዎስ።

ስለ ታዴዎስ ብለህ ማረን ይቅር በለን። ወልብድዮስ ዘተሰምየ ታዴዎስ ብሎ በእናቱ ወንጌል ያነበዋል፤ ታዴዎስ የተባለ ልብድዮስ ነው፤ ልብድዮስ ማለት ልብደ ሠሪ ዓሣ ወጋሪ ማለት ነው፤ አንድም ታዴዎስ ማለት ዘርዕ ወማዕረር ማለት ነው፤ ኦሪትን እንደ ዘር ወንጌልን እንደ መከር አድርጎ መስሎ ያስተምራልና። ይኸውም ሊታወቅ ጧት ስንዴ ዘርቶ ለማታ መሥዋዕት አድርሷልና። ይህስ እንደምንድን ነው ቢሉ ጴጥሮስና ታዴዎስ ለማስተማር በመንገድ ሲሄዱ አንድ ገበሬ በሬ ጠምዶ ሲያርስ አገኙ እባክህን ርቦናልና ምሳችንን አብላን አሉት፤ በሮቼን ማን ይይዝልኛል እንጂ አዘጋጅቼ አመጣላችሁ ነበር አላቸው፤ እኛ እንይዝልሃለን አሉት ምሳቸውን አዘጋጅቶ ይዞ እስኪመጣ ድረስ ታዴዎስ እያረሰ ጴጥሮስ እየዘራ ወዲያው አሸቶ አግኝቷል። ቀነተ ታዴዎስ ከመ ይሀርስ ገራኅተ፤ ወጴጥሮስ ዘርአ ሠላሳ አትልምተ፤ በቀለ ሶቤሃ ወኮነ ስዒተ፤ ሰብአ ሀገር አንከሩ እለ ርእዩ ዘንተ እንዳለ ደራሲ። አንድም ካህነ አምላክ

ማለት ነው፡፡ ወአምጽኡ ማሬ ዘድዮስ እንዲል፡፡ አንድም መምህረ አሕዛብ ወሕዝብ ማለት ነው፡፡

ወስምዖን፡፡

ስለ ስምዖን ብለህ ማረን ይቅር በለን፡፡ ወስምዖን ቀነናዊ ብሎ በእናቱ በወንጌል ያነበዋል፣ ስለ ስምዖን ብለህ ማረን ይቅር በለን፡፡ ቀነናዊ ቢል የቃና ሰው፤ ቀናዒ ቢል ለሕገ አምላኩ የሚቀና ናትናኤል ነው፡፡ ናትናኤል ማለት ውሁብ ሀብተ እግዚአብሔር ማለት ነው፡፡ አንድም ስምዖን ማለት ሰማዒ ማለት ነው፡፡

ወማትያን፡፡

ስለ ማትያን ብለህ ማረን ይቅር በለን፡፡ ማትያን ማለት ትክ ምትክ ፈንታ ማለት ነው፤ ማትያስም ይላል፡፡

ዐሠርቱ ወክልኤቱ ሐዋርያት፡፡

ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያት አማላጅ በማድረግ በእነሱ አማላጅነት ስለ እነሱ ብለህ ማረን ይቅር በለን፡፡ ስማቸውን አስቀድሞ ቁጥራቸው ወደ ኋላ አመጣው፡፡

ወያዕቆብ ሐዋርያ እኁሁ ለእግዚእነ ኤጲስ ቆጶስ ዘኢየሩሳሌም፡፡

በኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስነት የተሾመ የጌታችን ወንድም ስለሚሆን ያዕቆብ እኁሁን አማላጅ በማድረግ በእሱ አማላጅነት ስለ እሱ ብለህ ማረን ይቅር በለን፡፡ ኤጲስ ቆጶስ ዘኢየሩሳሌም አለ፤ ወኮነ እግሩ ከመ እግረ ገመል ወከመ እግረ ነጌ ይላል ከጾም ከጸሎት ከገድል ከትህርምት ብዛት የተነሣ እግሩ እንደ እግረ ግመል ሆኖበት ነበር፤ ሐዋርያት ለስብከተ ወንጌል አይፋጠንም ብለው በኢየሩሳሌም በኤጲስ ቆጶስ ሾመውት ሄደዋል፤ ከሐዋርያትስ አንዳንድ ደዌ የሌለው የለም ቅዱስ ጴጥሮስን ወኮነ ድውየ ወድግዱገ ሥጋ ይለዋል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም አዳጊት የምትባል ራስ ፍልጠት ቀጭን ሰጥር ውጋት ነበረችበት፤ ተውህበኒ መልአከ ሰይጣን ዘይደጕጸኒ ሥጋየ ወይኰርአኒ ርእስየ እንዲል፡፡[28] ያዕቆብስ እንደ እነሱ ደመና ጠቅሶ ካሰበበት ደርሶ አስተምሮ ብዙ ሰው አሳምኖ ቢውል ይቻለው የለምን ቢሉ? በኢየሩሳሌም ብዙ ምሁራነ ኦሪት ነበሩና እሱም ምሁረ ኦሪት ነውና የሀገሩን ሰርዶ

---

28 በብዙ ራእይ እንዳልታበይ ሰውነቴን የሚጎስም ራሴን የሚቀጠቅጥ የሰይጣን መልእክተኛ ተሰጠኝ፡፡ ፪ኛ ቆሮንቶስ ፲፪ ፡ ፯፣ ኢዮብ ፪ ፡ ፮

በሀገሩ በራ እንዲሉ እሱ ባወቀ ተከራክሮ ይርታቸው ብለው ትተውት ሄደዋል። አንድም ዕጣው እንደ ሆነች አውቀው ሾመውት ሄደዋልና፤ ኤጲስ ቆጶስ ዘኢየሩሳሌም አለ። እጉሁ አለ ጉንዱ አልዓዛር ነው አልዓዛር ማትያንና ቅስራን ይወልዳል፤ ቅስራ ኢያቄምን፤ ኢያቄም እመቤታችንን፤ እመቤታችን ጌታን ወለደች። ማትያን ደግሞ ያዕቆብን ይወልዳል፤ ያዕቆብ ዮሴፍን፤ ዮሴፍ ያዕቆብን ይወልዳል። በአንዣር ያለ ነውና እጉሁ አለ ለተዘምዶውስ እነዮሐንስ እነያዕቆብ ይቀርቡታል ብሎ ሐሊበ ድንግልናዊትን በአንድ እየጠቡ አድገዋልና እጉሁ አለ ሐሊበ ድንግልናዊትንስ ከጌታ በቀር ዕሩቅ ብእሲ መጥባት አይቻለውም ብሎ እናቱ በሕፃንነቱ ሞታበት እመቤታችን እንደ እናት ሆና ከጌታ ጋር አሳድጋዋለችና እጉሁ አለ።

ቅዱስ ወስቡሕ እስጢፋኖስ።

ንጹሕ ክቡር ምስጉን የሚሆን እስጢፋኖስን አማላጅ በማድረግ በእሱ አማላጅነት ስለ እሱ ብለህ ማረን ይቅር በለን። እስጢፋኖስ ማለት ወደብ፣ መደብ፣ ልሆቴ፣ ማኅቶተ ቁድ ማለት ነው።

ርእሰ ዲያቆናት።

የዲያቆናት አለቃቸው የሚሆን እስጢፋኖስን አማላጅ በማድረግ በእሱ አማላጅነት ስለእሱ ብለህ ማረን ይቅር በለን። እሱን መደበኛ አድርገው ስድስቱን አነው መርጠዋልና ርእሰ ዲያቆት አለ።

ወቀዳሜ ሰማዕት።

የሰማዕታተ ሐዲስ መጀመሪያቸው የሚሆን እስጢፋኖስን አማላጅ በማድረግ በእሱ አማላጅነት ስለእሱ ብለህ ማረን ይቅር በለን። ከጌታ ቀጥሎ ከሰማዕታተ ሐዲስ አስቀድሞ መከራ የተቀበለ እሱ ነውና።

ወበእንተ ቅዱሳን ወሰማዕት እለ አዕረፉ በርትዕት ሃይማኖት።

ነሣሣለትና ውሎ ውሎ ከቤት ኖሮ ኖሮ ከሞት እንዲሉ የጸናች የቀናች ሃይማኖታችንን አንለውጥም፤ ፈጣሪያችን እግዚአብሔርን አንክድም ብለው የሞቱ ጻድቃን ሰማዕታትን አማላጅ በማድረግ በእነሱ አማላጅነት ስለ እነሱ ብለህ ማረን ይቅር በለን።

Scanned by CamScanner

ጳውሎስ፡፡

ስለ ጳውሎስ ብለህ ማረን ይቅር በለን፡፡ ጳውሎስ ማለት ብርሃን ማለት ነው፡፡ ዘኀደሩ እስራኤል አንጻረ ኤጳውሎስ እንዲል፡፡[29] አንድም ምርጥ ዕቃ ማለት ነው፤ እስመ ንዋየ ኅሩየ ረሰይክዎ ሊተ ከመ ይጹር ስምየ[30] እንዲል ፡፡

ጢሞቴዎስ፡፡

ስለጢሞቴዎስ ብለህ ማረን ይቅር በለን፡፡ ጢሞቴዎስ ማለት ዘአልቦ ጥሪት ዐምዳ ውድዳ ለጽድቅ ማለት ነው፡፡

ሲላስ፡፡

ስለ ሲላስ ብለህ ማረን ይቅር በለን፡፡ ሲላስ ማለት ጸያሔ ብርሃን ማለት ነው፤ ሲላን እንዲል ዐረብ፡፡

ወበርናባስ፡፡

ስለበርናባስ ብለህ ማረን ይቅር በለን፡፡ በርናባስ ማለት ወልደ ፍሥሐ ማለት ነው፤ በአረብ በር ልጅ ማለት ነው፤ ናባስ ማለት ፍሥሐ ማለት ነው፡፡

ቲቶ፡፡

ስለ ቲቶ ብለህ ማረን ይቅር በለን፡፡ ቲቶ ማለት ሠርቅ ማለት ነው፡፡ በመርሐ ዕውር መስከረምን ሠርቀ ቲቶ እንዲለው፡፡

ፊልሞና፡፡

ስለ ፊልሞና ብለህ ማረን ይቅር በለን፡፡ ፊልሞና ማለት ሥውር ቦታ ማለት ነው፤ ፌላሌምሊሞን ይላል ሥውር ማለት ነው፡፡

ወቀሌምንጦስ፡፡

ስለ ቀሌምንጦስ ብለህ ማረን ይቅር በለን፡፡ ቀሌምንጦስ ማለት የጸና ግንብ ማለት ነው፡፡

---

29 ኦሪት ዘጸአት ፲፬ ፡ ፪

30 ስሜን ይሸከም ዘንድ ለኔ የተመረጠ ዕቃ አድርጌዋለሁና፡፡ ሐዋርያት ሥራ ፱ ፡ ፲፭

ሰብዓ ወክልኤቱ አርድዕት፡፡

ነሣሣለትና ሰባ ሁለቱን አርድዕት አማላጅ በማድረግ በእነሱ አማላጅነት ስለእነሱ ብለህ ማረን ይቅር በለን፡፡

ኀምስቱ ምዕት ቢጽ፡፡

ከእግረ መስቀሉ እንደ አሸን የፈሉ ከአምስት መቶ ብቅ ከስድስት መቶ ዝቅ ያሉ በዕለተ ዓርብ የተነሡ ወንድሞች ናቸው፤ እነዚህን አማላጅ በማድረግ በእነዚህ አማላጅነት ስለ እነዚህ ብለህ ማረን ይቅር በለን፡፡

ሠለስቱ ምእት ዐሠርቱ ወሰመንቱ ርቱዓነ ሃይማኖት፡፡

ሃይማኖታቸው የጸና ምግባራቸው የቀና ለአውግዞተ አርዮስ የተሰበሰቡ ሦስት መቶ ዐሥራ ስምንቱን ሊቃውንት አማላጅ በማድረግ በእነሱ አማላጅነት ስለእነሱ ብለህ ማረን ይቅር በለን፡፡

ለእሉኒ፡፡

እስካሁን ሲናገራቸው የመጡትን፤

ወለኵሎሙ፡፡

እንግዲህ ወደ ፊት የሚያመጣቸውን፤ አንድም ለእሉኒ፡፡ አብያተ ክርቲያናት የተሠራላቸውን መጽሐፍ የተጻፈላቸውን፤ ወኵሎሙ፡፡ ይህ ሁሉ ያልተደረገላቸውን፤ አንድም ለእሉኒ፤ ለኪዳን ለቁርባን ለቅዳሴ ለውዳሴ የሚፋጠኑትን ልዑካኑን፤ ወኵሎሙ፡፡ ዕጣን ቋጥረው መባ ይዘው ግብር ሰፍረው ወደ ቤተ እግዚአብሔር የሚሄዱትን ሕዝቡን አስባቸው፡፡ አንተን ያገለግሉ ዘንድ አስባቸው፡፡

ተዘከሮሙ ለከ እግዚኦ ለብፁዕ ወለቅዱስ ሊቀ ጳጳስነ አባ እገሌ ወብፁዕ ጳጳስነ አባ እገሌ፡፡

የጳጳሳቱን አለቃ አባ እገሌን ጳጳሱን አባ እገሌን አንተን ያገለግሉ ዘንድ አስባቸው፡፡

ከመ ትዕቀቦሙ በሕይወቶሙ፡፡

በሕይወተ ሥጋ በሕይወተ ነፍስ ትጠብቃቸው ዘንድ፤ ምነው ከአንተ በቀር ሌላ ጠባቂ አላቸውን ዕቀቦሙ አንተው ጠብቃቸው፡፡

ወታድኅኖሙ::

ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ ታድናቸው ዘንድ፤ ምነው ከአንተ በቀር ሌላ የሚያድናቸው አለን? አድኅኖሙ አንተው አድናቸው::

ወትሥረይ ሎሙ ኀጢአቶሙ::

ኀጢአታቸውን ታስተሥርይላቸው ዘንድ፤ ምነው ከአንተ በቀር ሌላን የሚያስተሠርይላቸው አለን? አስተሥሪ ሎሙ አንተው አስተሥርይላቸው::

ወትምሐረነ ኪያነሂ በጸሎተ ዚአሆሙ::

ትምሐረነም ካለ ለነ ኪያነም ካለ ትምሐር ባለ በቀና ነበር ልማደ መጽሐፍ ነው:: እኛንም በእነሱ ጸሎት ትምረን ይቅር ትለን ዘንድ ጠብቀን:: አንድም ማሰብ መጠበቅ ማዳን ኃጢአትን ማስሥረይ ሌላ አለን በእነርሱ ጸሎት ማረን ይቅር በለን::

ለዓለመ ዓለም::

ለዘለዓለሙ፤

አሜን::

በእውነት ያለ ሐሰት::